# የ2022 የዲሲ የህጻናት ክብካቤ አቅራቢ የዳሠሳ ጥናት

## በተደጋጋሚ የሚነሡ ጥያቄዎች

### አጠቃላይ ጥያቄዎች

**የ2022 የዲሲ የህጻናት ክብካቤ አቅራቢ የዳሠሳ ጥናት ምንድን ነው?**

የ2022 የዲሲ የህጻናት ክብካቤ አቅራቢ የዳሠሳ ጥናት የዲሲን የህጻናት ክብካቤ አቅራቢዎችን ወጪዎች እና ገቢዎች በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት በግዛቱየትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት (OSSE) ፈቃድ በተሠጣቸው የህጻናት ማሳደጊያ ተቋማት ላይኔ ከዲሲ የልጅ እንክብካቤ ግንኙነቶች (DC Child Care Connections) እና ፕሬናታል ቱ ፋይቭ ፊስካል ስትራቴጂስ (Prenatal to Five Fiscal Strategies, P5FS) ጋር በመተባበር በኦንላይን የሚሠራ የዳሠሳ ጥናት ነው። በዚህ የዳሠሳ ጥናት የሚሠበሠቡ መረጃዎችን OSSE ወደፊት ተፈጻሚ የሚደረጉ የህጻናት ክብካቤ ድጎማ የወጪ ተመላሽ መጣኔዎችን እንዲሁም በ2024 የበጀት ዓመት እና ከዚያ በኋላ የሚኖረውን የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ እኩልነት ፈንድ (Early Childhood Educator Pay Equity Fund) አፈጻጸም ለማሳወቅ ይጠቀምባቸዋል።

**OSSE ይህን የዳሠሳ ጥናት የሚሠራው ለምንድን ነው?**

የህጻናት ማሳደጊያ ተቋማት ስራ የሚበዛባቸው መሆኑን እና በርካታ ነገሮችን እንዲያከናውኑ የሚጠየቁ መሆኑን እናት በአሁኑ ወቅት (በ2022 የበልግ ወቅት) ይህን የዳሠሳ ጥናት መስራት ስላስፈለገበት ምክንያት በርካታ ጥያቄዎች ሊኖራቸው እንደሚችል OSSE ያውቃል። ለዚህ ሁለት ዋና ዋና ጥያቄዎች አሉ: አንደኛው ምክንያት የህጻናት ክብካቤ የድጎማ ክፍያ መጣኔዎችን በተመለከተ የህጻናት ክብካቤ አገልግሎቶችን ለመስጠት በየሶስት ዓመቱ የሚፈለጉትን የፌደራል መስፈርቶች ለማሟላት OSSE የኛን የወጪ ትንተና ወቅታዊ እንዲያደርግ በፌደራል መንግስት ይጠየቃል። ከዳሠሳ ጥናቱ የሚገኘው መረጃ የሚፈለገው አገልግሎቱን ለመስጠት ያስፈልጋሉ ተብለው የተቀመጡትን ግምታዊ ወጪዎች ወቅታዊ ለማድረግ እና ወደፊት ተፈጻሚ የሚደረጉትን የድጎማ የወጪ ተመላሽ መጣኔዎችን ለማሳወቅ ነው። ሁለተኛው ምክንያት ከ2024 የበጀት ዓመት ጀምሮ OSSE የማሟያ ክፍያዎችን በቀጥታ ለቅድመ ልጅነት መምህራን ከማከፋፈል ይልቅ የቅድመ ልጅነት የክፍያ እኩልነት ግብረ ኃይል (Eartly Childhood Pay Equity Task Force) ያስቀመጣቸውን የውሳኔ ሀሳቦች የሚያንጸባርቁትን የሠራተኛ ደመወዝ ለመክፈል ለተስማሙት የገንዘብ ሽፋን ለሚያደርጉ የህጻናት ክብካቤ አቅራቢዎች የመክፈል ለውጥ የሚያደርግ መሆኑ ነው። የክፍያ መጠኖቹ ለህጻናት ክብካቤ አቅራቢዎች ዘላቂነት ባለው መልኩ የደመወዝ ክፍያ ርከኖችን መጠን ለመሸፈን በቂ መሆናቸውን ለማረጋገጥ OSSE በህጻናት ክብካቤ አቅራቢዎች ወጪዎች እና ክፍያ የሚፈጽሙ ቤተሠቦች እንዲከፍሉ በሚጠየቋቸው የትምህርት ክፍያ መጠኖች ላይ ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ይፈልጋል። የ2022 የዲሲ የህጻናት ክብካቤ አቅራቢ የዳሠሳ ጥናት በአሁኑ ወቅት የቅድመ ልጅነት መምህራን የሚከፈላቸውን የደመወዝ ክፍያ መጠን እንዲሁም የህጻናት ማሳደጊያ ተቋማት በትምህርት ክፍያ መልክ የሚሰበስቡትን የገቢ መጠን እና በመላው ዲስትሪክቱ ውስጥ የሚገኙ የህጻናት ክብካቤ ተቋማት በሚገኙበት መልክዓ ምድራዊ አካባቢ እና በአደረጃጀታቸው ዓይነት ላይ በመመስረት በሚከፍት ክፍያ እና በሚሰበስቡት የትምህርት ክፍያ መጠን መካከል ያሉትን ልዩነቶች OSSE ለመረዳት እንዲችል ያግዙታል።ይህ መረጃ የህጻናት ክብካቤ የንግድ ስራዎችን ዘላቂነት ለመደገፍ የሚያስችሉ የ OSSEን ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች ለመንደፍ እና ለማስፈጸም ፋይዳው ከፍተኛ ነው።

**ይህን የዳሰሳ ጥናት የሚያከናውነው ማነው?**

ይህ የደሰሳ ጥናት የሚመራው ከOSSE ጋር ውል ከገባው ከዲሲ የልጅ እንክብካቤ ግንኙነቶች (DC Child Care Connections) ጋር በመተባበር በህጻናት ክብካቤ ፋይናንስ፣ ፖሊሲ እና ምርምር ሀገር አቀፍ መሪ በሆነው በP5FS ነው።

**በዳሰሳ ጥናቱ ላይ መሳተፍ ያለበት ማነው?**

በአሁኑ ወቅት የህጻናት ክብካቤ ድጎማዎችን እየተቀበላችሁ ሆነም አልሆነ፣ የህጻናት ማሳደጊያ ማዕከላትን፣ የህጻናት ማሳደጊያ ቤቶችን እና የተስፋፉ የህጻናት ማሳደጊያ ቤቶችን ጨምሮ በዲሲ ውስጥ ከሚገኙ ከሁሉም የህጻናት ማሳደጊያ ተቋማት ግብዓት ማግኘት እንፈልጋለን።

የዳሰሳ ጥናቱ በፕሮግራም ዳይሬክተሩ፣ በተቋሙ ባለቤት//አቅራቢ፣ የፋይናንስ ስራ አስኪያጅ ወይም ስለፕሮግራማችሁ ፋይናንስ የላቀ እውቀት ባለው በማናቸውም ሰው ቢሞላ መልካም እንደሆነ ምክረ ሀሳባችንን እናቀርባለን።

**ኦንላይን የሚሞላውን የዳሰሳ ጥናት ማስፈንጠርያ ከየት አገኛለሁ?**

ማስፈንጠርያው በ OSSE ማህደር ውስጥ ለተመዘገበው ለተቋማችሁ ተጠሪ ተልኮ ነበወ። እርስዎ የተቋሙ ተጠሪ ከሆኑ እና የዳሳ ጥናቱን ማስፈንጠርያ የያዘውን የኢሜይል መልእክት እስካሁን ድረስ ካላዩት፣ ወደ "spam" ወይም "junk" ማህደር ማቀፊያዎች /ፎልደሮች ውስጥ ገብቶ ሊሆን ይችላል፤ በመሆኑም እባክዎ እነዚያ ውስጥ ይመልከቱት። ይህንንም አድርገው የዳሰሳ ጥናቱን ማስፈንጠርያ ማግኘት ካልቻሉ፣ እባክዎ ለP5FS የዳሰሳ ጥናት ቡድን በዚህ አድራሻ info@prenatal5fiscal.org ኢሜይል ያድርጉ እና ማስፈንጠርያውን ደግመን እንልከልዎታለን።

**እኔ መሳተፍ ይኖርብኛል?**

የለብዎትም። በዚህ የዳሰሳ ጥናት ላይ ተሳትፎ የሚደረገው በበጎ ፈቃደኝነት ነው። ይሁን እንጂ እርስዎ የሚሰጧቸው ምላሾች ለህጻናት ክብካቤ ድንግዎች ወደፊት ተፈጻሚ የሚደረጉትን የወጪ ተመላሽ መጣኔዎችን እና በዲስትሪክቱ ወስጥ የሚገኙትን የህጻናት ክብካቤ የንግድ ስራዎች ለማገዝ የሚያፈልጉትን ሌሎች የOSSE ፕሮግራሞችን እና ፖሊሲዎችን ለመንደፍ እና ለማስፈጸም ያግዛሉ። በመሆኑም ምንም መሳተፍዎ ግዴታ ባይሆንም፣ እርስዎ የሚያርጉት ተሳትፎ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው እና በከፍተኛ ደረጃ የሚደነቅ ነው።

**የዳሰሳ ጥናቱን በመሙላቴ የማገኘው ማንኛውም ነገር አለ?**

አዎ፣ የዳሰሳ ጥናቱን የሚሞሉ አቅራቢዎች ለሰጡት ጊዜ ለማመስገን ያህል የ$20 የስጦታ ካርድ ይሰሰጣቸዋል። በተጨማሪም የእርስዎ ንብረት የሆነው//እርስዎ የሚመሩት ተቋም ለሚያስፈልጉት የትምህር አቅርቦቶች የ$1,000 የስጦታ ምስክር ወረቀት እንዲያሸንፍ ወደ Kaplan የሎተሪ ውድድር ወስጥ እንዲገባ ይደረጋል። የሥቶታ ካርዱ ህዳር 15 የሚደርስዎ ሲሆን የሎተሪ አሸናፊዎቹ በህዳር ማህበረሰብ የተግባር ስብሰባ (November Community of Practice Meeting) ላይ ይፋ ይደረጋሉ።

**የምጠየቃቸው ጥያቄዎች ምን ምንድን ናቸው?**

የዳሰሳ ጥናቱ የሚጠይቀው በእርስዎ ተቋም ስላለው ምዝገባ፣ ገቢ እና ወጪዎች (ለምሳሌ የሰራተኛ ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅም፣ ኪራይ/የቤት ብድር፣ አቅርቦቶች፣ መሳርያ፣ ወዘተ) ነው። እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ እንዲያግዝዎት፣ በጣም የቅርብ ጊዜ ከሆነው ከፕሮግራማችሁ የበጀት ዓመት የህጻናት ምዝገባን፣ የትምህርት ክፍያ መጣኔዎችን፣ ደመወዝን/የደመወዝ መክፈያ ሰነዶችን እና ሌሎች ወጪዎችን የሚመለከቱ ማናቸውንም ምዝገባዎች በመጀመርያ እንዲሰበስቡ እንመክርዎታለን።

**የዳሰሳ ጥናቱን መሙላት ከመጀመሬ በፊት መሰብሰብ ያለብኝ የትኞቹን የፋይናንስ ሰነዶች ወይም ሌሎች ሰነዶችን ነው?**

የዳሰሳ ጥናቱ ስለምዝገባ፣ ስለሠራተኛ አስተዳደር ወጪዎች እና የሰራተኛ አስተዳደር ስላልሆኑ ወጪዎች ይጠይቃል። በመሆኑም በጣም የቅርብ ጊዜ ከሆነው ከፕሮግራማችሁ የበጀት ዓመት ማናቸውንም የደመወዝ ሰንጠረዥ/የደመወዝ ክፍያ ሪፖርቶችን፣ የምዝገባ ሪፖርቶችን እና የበጀር/የሂሳብ መግለጫዎችን እንድትሰበስቡ እንመክራለን። የህጻናት ማሳደጊያ ቤት አቅራቢዎች የናንተን የቅርብ ጊዜ ሰንጠረዥ ሐ/Schedule C የታክስ ቅጽ ማቅረብ አብዛኛውን ጊዜ ጠቃሚ ሆኖ ይገኛል።

**የዳሰሳ ጥናቱ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?**

የእርዎን የማመሳከርያ ሰነዶች/ምዝገባዎች በቅድሚያ ከሰበሰቡ፣ አንድን ዳሰሳ ጥናት ሞልቶ ለማጠናቀቅ የሚወስደው አማካይ ጊዜ ከ20 እስከ 25 ደቂቃ ነው። በዳሰሳ ጥናቱ ውስጥ የትምህርት ክፍያ መጣኔ//የክፍያ ሰንጠረዦችን መጫን የሚችሉበት ቦታ አለ ወይም ለ P5FS ቡድን ኢሜይል ሊያደርጉት ይችላሉ። ይህን ካደረጉ፣ የክፍያ መጣኔዎችን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ሁሉ ሊያልፏቸው ይችላሉ (ስለዚህ የዳሰሳ ጥናቱ የሚወስደው ጊዜ በጣም ያነሰ ይሆናል ማለት ነው)።

**የዳሰሳ ጥናቱን መሙላት ከተጀመረ በኋላ አቋርጦ እንደገና ተመልሶ በመምጣት መጨረስ የሚቻልበት አማራጭ አለ?**

አዎ፣ የኦንላይን ስርዓቱ ለዳሰሳ ጥናቱ መላሾች ምላሾቻቸውን ሴቭ አድርገው ከወጡ በኋላ ተመልሰው እንዲገቡ ይፈቅድላቸዋል። ይህ አማራጭ የሚገኘው በኦንላይን የዳሰሳ ጥናቱ ስርዓት ውስጥ በስክሪኑ ራስጌ በስተቀኝ በኩል ነው። ወደዳሰሳ ጥናቱ ለመመለስ ዝግጁ በሚሆኑበት ጊዜ ቀደም ሲል የተላከልዎት ማስፈንጠርያ ላይ ክሊክ ማድረግ ይችላሉ።

**የኔ ምላሾች ሪፖርት የሚደረጉት ወደየት ነው?**

አቅረቃቢዎች የሰጧቸውን ዝርዝር መረጃዎች ማየት የሚችሉት የP5FS ቡድን አባላት ብቻ ናቸው። የ P5FS ቡድን ከአቅራቢዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በሙሉ በምስጢር እና ደህንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ የተያዙ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። ከሁሉም አቅራቢዎች የተሰበሰቡ እና የተቀናጁ እንዲሁም ማንነትን ለይተው ሊገልጹ የሚችሉ ግላዊ መረጃዎች ተለይተው እንዲወጡ የተረገባቸው መረጃዎች ብቻ OSSEን ጨምሮ ከP5FS ቡድን ውጪ ለሆነ ለማናቸውም ሰው የሚጋሩ ይሆናል። የማናቸውንም የህጻናት ማሳደጊያ ማዐከል ወይም ቤት ምላሾች አናትምም//አናሳትምም።

**የህጻናት ክብካቤ አቅራቢዎች በዚህ የዳሰሳ ጥናት ላይ መሳተፍ ያለባቸው ለምንድን ነው?**

ፕሮግራምዎን በተመለከተ በዳሰሳ ጥናቱ ላይ በመሳተፍ እና መረጃዎችን በምስጢር በማጋራት፣ የክብካቤ አገልግሎትን ለመስጠት በሚያስፈልጉ ወጪዎች ላይ በመመስረት ወደፊት ተፈጻሚ ስለሚደረጉ የድጎማ ወጪ ተመላሽ መጣኔዎች እና የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ እኩልነት ፈንድn (Early Childhood Educator Pay Equity Fund) በተመለከተ ዲሲ ለሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች መረጃ በመስጠት ያግዛሉ። ከፍተኛ ጥራት ያለው የህጻናት ክብካቤ አገልግሎቶችን ለመስጠት በትክክል ምን ያህል ወጪ እንደሚያስወጣ እና አሁን የሚመደቡት ሀብቶች ይህን ወጪ ምን ያህል እንደሚሸፍኑ (ወይም እንደማይሸፍኑ) ፖሊሲ አውጪዎች መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የዳሰሳ ጥናቱ እነዚህን መረጃዎች በትክክል በህጻናት ክብካቤ ላይ ከሚሰሩ አካላት ማግኘቱ ወሳኝ ነው። ይህ የዳሰሳ ጥናት ስኬታማ እንዲሆን፣ ዲሲ ውስጥ በሁሉም አካባቢ ካሉ ከሁሉም ዓይነት አቅራቢዎች መረጃ ማግኘት አስፈላጊ ነው።

**የኔ ፕሮግራም የህጻናት ክብካቤ ድጎማዎችን አያገኝም። ታድያ በዚህ የዳሰሳ ጥናት ላይ ለምን እሳተፋለሁ?**

ከፌደራሉ የህጻናት ክብካቤ እና ልማት ፈንድ መስፈርቶች ጋር የተጣጣመው የOSSE ግብ የህጻናት ክብካ ድጎማዎችን የሚያገኙ ህጻናት የተለያዩ የህጻናት ክብካቤ ፕሮግራሞችን እና አማራጮችን ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ የሚያገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። ድጎማ ከሚያገኙትና ከማያገኙት ከሁለቱም ዓይነት የህጻናት ክብካቤ አቅራቢዎች መረጃዎችን በመሰብሰብ ዲስትሪክቱ እኩል ተደራሽነትን የሚያረጋግጥ የህጻናት ክብካቤ የድጎማ መጣኔዎችን የሚወስን መሆኑን ማረጋገጥ እንችላለን።

በተጨማሪም ከህጻናት ክብካቤ የድጎማ መጣኔዎች ውጪ በዚህ የዳሰሳ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች የተለያዩ የ OSSEን የህጻናት ክብካቤ ፖሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችም እና ሙከራዎችን ለማሳወቅ ይረዳሉ። ለምሳሌ የህጻን-አዋቂ ጥምርታ፣ የሰራተኞች ብቃት እና ሌሎች የፈቃድ መስጫ መስፈርቶች የህጻናት ክብካቤ አቅራቢዎች አገልግሎት ለመስጠት በሚያስፈልጋቸው ወጪ ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድር ለመረዳት OSSE ከዲሲ የልጅ እንክብካቤ ወጪ ግምት ሞዴል (DC Child Care Cost Estimation Model) ጋር የዳሰሳ ጥናት መረጃዎችን ይጠቀማል። በተመሳሳይ ሁኔታ በዳሰሳ ጥናቱ የተሰበሰበው መረጃ የተቀርጾ በ2024 የበጀት ዓመት መቀረጹን እና ተፈጻሚ የሚደረግ መሆኑን ለማሰወቅ ያግዛል። ድጎማ በሚያገኙም ሆነ በማያገኙ በሁለቱም ዓይነት የህጻናት ማሳደጊያ ተቋማት ውስጥ ለሚሰሩ የቅድመ-ልጅነት መምህራን በተቀመጠው የክፍያ እርከን መሰረት ክፍያቸውን ለማሳደግ የሚፈልገው ይህ ፕሮግራም ከ2024 የበጀት ዓመት ጀምሮ በአሁኑ ወቅት እርስዎ የህጻናት ክብካቤ ድጎማዎችን የሚቀበሉ ሆኑም አልሆኑ ለሰራተኞቻቸው በ OSSE በወጣው የክፍያ እርከን መሰረት ለመክፈል ለተስማሙ የህጻናት ማሳደጊያ ተቋማት ፈንዶችን ያከፋፍላል። በዚህ የዳሰሳ ጥናት እርስዎ የሚሰጡት መረጃ የእረስዎ ተቋም ከቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ እኩልነት ፈንድ (Early Childhood Educator Pay Equity Fund) ምን ያህል ፈንድ ማግኘት ማግኘት እንደሚችል ለመወሰን የሚያስፈልገውን የፈንድ ቀመር OSSE እንዲያዘጋጅ ያግዘዋል።

በመጨረሻም የህጻናት ክብካቤ ድጎማዎችን ማግኘት የማይችሉ በርካታ ቤተሰቦች አሁንም በዲስትሪክቱ ውስጥ ከወጪ አንጻር ተመጣጣኝ የህጻናት ክብካቤ ለማግኘት ወይም ለመረጡት የህጻን ክብካቤ አማራጭ ክፍያ ለመፈጸም አሁንም እየታገሉ መሆኑን እናውቃለን። እርስዎ የሚሰጡት መረጃ ለOSSE እና ሌላ የዲስትሪክቱ መንግስት እና የግል ባለ ድርሻ አካላት ለአብዛኞቹ የዲሲ ቤተሰቦች የህጻናት ክብካቤ ተደራሽ እና ተመጣጣኝ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶች መንገልበታቸውን ለማሳወቅ ያግዛቸዋል።

## የዳሰሳ ጥናት ጥያቄዎች

**እኔ በርካታ ተቋማትን የምመራ አቅራቢ ነኝ፣ የዳሰሳ ጥናቱም መሙላት የምችለው እንዴት ነው?**

በዲሲ ውስጥ ላሉዎት ለሁለም ተቋማት የዳሰሳ ጥናት ሞልተው እንዲያጠናቅቁ እንጠይቃለን። ሶስት ወይም ከዚያ በላይ ተቋማት ካሉዎት፣ ስለተቋማቱ ያሉዎትን መረጃዎች በቨርቿል ቃለ መጠይቅ ማጋራት ለእርስዎ ቀላል ነው። የP5FS ቡድን OSSE ቃለ መጠይቅ እንዲያመቻችለት በማድረግ ከእረስዎ ድርጅት ተጠሪ ጋር ግንኙነት ያደርጋል። ይህ መረጃ ካልደረሰዎት፣ እባክዎ የእርስዎን የጥራት አ፣ አመቻች (Quality Facilitator) (በCapital Quality ላይ የሚሳተፉ ከሆነ) ይጠይቁት ወይም ለP5FS ቡድን በዚህ አድራሻ info@prenatal5fiscal.org ኢሜይል ያድርጉ እና ከፕሮጀክት ቡድናችን አንድ ሰው ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ያናግርዎታል።

**መሙላት ከመጀመሬ በፊት የዳሰሳ ጥናቱን ጥያቄዎች ማየት እችላለሁ?**

የዳሰሳ ጥናቱን በPDF የተዘጋጀ አንድ ቅጂ እዚህ (የድረገጽ ማስፈንጠርያ ያስገቡ) ማግኘት ይችላሉ። ይህ በ PDF የተዘጋጀው ለሁሉም ዓይነት አቅራቢዎች የተዘጋጁትን ሁሉን ጥያቄዎች ያካተተ ሲሆን ኦንላይን የሚቀርበው ግን የዳሰሳ ጥናት ግን ለእርስዎ የማይሆኑትን የመዝለል (“skip logic”) ይጠቀማል፣ ይህ ማለት እርስዎ የሚያዩዋቸው ጥያቄዎች ቀደም ሲል ለነበሩት ጥያቄዎች በሰጡት መልስ ላይ ተመስርተው ነው፤ ስለዚህ፣ የዳሰሳ ጥናቱን ኦንላይን ለመሙላት ሲሄዱ የሚያዩዋቸው ጥያቄዎች ለእርስዎ የፕሮግራም አገልግሎቶች አግባብነት ያላቸውን ብቻ ነው። ስለሆነም በPDF በተዘጋጀው ውስጥ ያዩዋቸውን የተወሰኑ ጥያቄዎች ሳያዩ ሲቀሩ እባክዎ ግራ አይገጋቡ። በPDF የተዘጋጀው ቅጂ ጥቅም ላይ መዋል ያለበት ጥያዌቆችን ለመገምገም እንደሚያግዝ የመጠይቅ ወረቀት ብቻ እና የኦንላይን የዳሰሳ ጥናቱን በመጠቀም የሚያቀርቧቸውን ምላሾች ለማቀድ ነው።

**የዳሰሳ ጥናቱን ለመረዳት የሚያስፈልጉ ተያያዥ ወጪዎች አሉ?**

የዳሰሳ ጥናቱ በተቀዳሚነት የሚያተኩረው የሰራተኛ አስተዳደር ወጪዎች ላይ ነው - ለሰራተኞች የሚከፈል ክፍያ፣ የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች ምንነት፣ ጥቅማ ጥቅም ለመስጠት የሚኖሩ ወጪዎች እና የሰው ኃይል ሁኔታዎች። ከጥናቱ እና የበላይ ተቆጣጣሪ በሆኑ ፕሮግረሞች ላይ ባለን በራሳችን የግል የህይወት ልምድ በሁሉም የፕሮግራም ወጪዎች ላይ ቁልፍ የሆኑ ልዩነቶች እንዳሉ እናውቃለን። የዳሰሳ ጥናቱም የሰራተኛ አስተዳደር ስላልሆኑ ዋና ዋና ወጪዎች ለምሳሌ ይዞታ፣ አቅርቦቶች፣ ወዘተ ጥያቄዎችን ይጠይቃል።

**በኔ ስም ሌላ ሰው ለምሳሌ አሰልጣኜ የዳሰሳ ጥናቱን መሙላት ይችላል?**

አዎ፣ ማናቸውም ሰው የዳሰሳ ጥናቱን መሙላት ይችላል፤ ነገር ግን ሁሉንም ጥያቄዎች ለመመለስ የእናንተን ፕሮግራም የፋይናንስ መረጃ፣ የፕሮግራም ምዝገባ እና የትምህርት ክፍያ መጣኔ//የክፍያ ሰንጠረዥ ማግኘት አለበት።

**ከጥያቄዎቹ አንዱን መመለስ ባልችልስ፣ ምን ይከሰታል? ግምታዊ መረጃ መስጠት አለብኝ?**

የአንድን ወጪ ትክክለኛ የገንዘብ መጠን በተመለከተ እርግጠና ካልሆኑ ነገር ግን ወጪውን መገመት የሚችሉ ከሆነ፣ ግምታዊውን መጠን ያስገቡ። ከጥያቄዎቹ መካከል የተወሰኑት (ከጥያቄው ቀጥሎ በዚህ * ምልክት እንዲ፤ዩ በተደረጉት መሰረት) አስፈላጊ ናቸው፣ ስለሆነም ወደ ቀጣዩ ጥያቄ ለማለፍ ለነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ይኖርብዎታል። መልሱን ካላወቁት ወይም አግባብነት የሌለው ከሆነ፣ እባክዎ “አ/የ” ወይም 0 ያስገቡ እና ከተቻለ ነገሩን ለማብራራት የአስተያየት ሳጥኖቹን ይጠቀሙ።

**በዳሰሳ ጥናቱ ውስጥ በሰራ መደብ መጠርያዎች የተወከሉ የተለያዩ በርካታ ኃላዲነቶችን የሚወጡ ሠራተኞች አሉኝ። የነሱን መረጃ ማስገባት ያለብኝ እንዴት ነው?**

በየኃላፊነቶቹ ለመከፋፈል ከሞመከር ይልቅ እባክዎ አብዛኛውን ጊዜ የሚሰሩበትን ኃላፊነት ይምረጡ እና የደመወዝ መረጃ ያስገቡ። በይበልጥ ግልጽ ለማድረግ በአስተያየት ክፍል ውስጥ ማብራሪያ መስጠትም ይችላሉ።

## ድጋፍ

**ጥያቄዎች ካሉኝ ወዴት ነው የምሄደው?**

ስለዚህ የዳሰሳ ጥናት ማናቸውም ጥያቄዎች ካለዎት ወይም ቴክኒካዊ ድጋፍ የሚፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎ በዚህ አድራሻ info@prenatal5fiscal.org ለP5FS ኢሜይል ያድርጉ ወይም በስልክ ቁጥር (202) 780-9078 ይደውሉ ወይም የጽሁፍ መልእክት ይላኩ።